ለ2021 ኢንተርናሽናል ቻይኒዝ-ስፒኪንግ ኮንፍረንስ ቁልፍ መግለጫዎች

በመንፈሳችን መሠረት በሆነው በሕይወት ዛፍ ለመኖር
በሕይወት መንገድ መመላለስ እንጂ
በእኔነት መሠረት በሆነው በትክክል እና በስህተት የእውቀት ዛፍ ለመኖር
በሞት መንገድ መመላለስ የለብንም።

የቤተ ክርስቲያን ሕይወታዊ አገልግሎት ለክርስቶስ ሕይወታዊ አካል፣
ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላት ለሆነችው ለቤተ ክርስቲያን መገንባት ነው።

አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ወደ የክርስቶስ አካል ኅብረት
ውስጥ ለማምጣት ሐዋርያትን መምሰል እና ቅዱሳንን ሁሉ ወደ መላው የክርስቶስ አካል
የመገጣጠም ሕይወት ውስጥ ለማምጣት የሐዋርያትን ዱካ የምንከተል መሆን አለብን።

የሐዋርያት ትምህርት ዋናው ነጥብ የሚያተኩረው ሦስታንዱ አምላክ ራሱን ሁሉን-እንዳካተተው ሕይወት-እንደሚሰጠው መንፈስ ወደ
መረጣቸው ሰዎች ውስጥ ለማደል በሂደት ማለፉን ነው፣ ይኸውም መለኮታዊውን መተላለፍ ለመቀበል ወደ ሕይወታዊ ጥምረት
ውስጥ ይመጡ ዘንድ እና የእግዚአብሔር ልጆች እና የክርስቶስ ብልቶች ይሆኑ ዘንድ ነው፤
በውጤቱም፣ ክርስቶስን ለመግለጥ የክርስቶስ አካል ይሆናሉ።

*© 2021 Living Stream Ministry*

**ለኢንተርናሽናል ቻይኒዝ ስፒኪንግ ኮንፈረንስ**
**መልዕክቶች የተዘጋጁ አውትላይኖች**
**የካቲት 6-7፣ 2013**

**አጠቃላይ ርዕስ፦**
**እንደ የክርስቶስ አካል የቤተ ክርስቲያን**
**ውስጠ-መሠረታዊ እና ሕይወታዊ ግንባታ**

መልዕክት አንድ

**ለሕይወታዊ ሕልውናዋ የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ ውስጠ-ነገር**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ 1 ዮሐ. 1፡2፤ ዮሐ. 1፡12-13፤ 3፡29-30፤ 12፡24፤ ዘፍ. 2፡21-23፤ 1 ቆሮ. 12፡12፣28

**I. የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ ውስጠ-ነገር ቤተ ክርስቲያንን የሚያፈራው መለኮታዊው ሕይወት ነው—1 ዮሐ. 1፡2፤ 5፡1፦**

ሀ. የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ ውስጠ-ነገር በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ ወደ ውስጣችን ያደለው እና አሁን እያደለ ያለው የማይጠፋው፣ መለኮታዊ ሕይወት ነው፤ ይህ መለኮታዊ ሕይወት በእውነቱ በሂደት ያለፈውና አሁን-የሚያድለው ሦስታንዱ አምላክ ነው—ዮሐ. 14፡6፤ 10፡10፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ሮሜ 8፡2፣ 10፣ 6፣ 11፤ 2 ቆሮ. 5፡4፦

1. በመንፈሳችን ውስጥ ባለው መንፈስ ዳግም መውለድ አማካኝነት መለኮታዊው ሕይወት ያፈራናል፤ መለኮታዊው መንፈስ የሰውን መንፈስ ይወልዳል፣ እነዚህም ሁለት መንፈሶች እንደ አንድ ይዋሐዳሉ—ዮሐ. 3፡3፣ 5-6፤ ሮሜ 8፡16፤ 1 ቆሮ. 6፡17።
2. ዳግም ስንወለድ የአዳም አምሳያ በሆነችው በሔዋን እንደተመሰለችው የሙሽራው ክርስቶስ ሙሽራ፣ [ለክርስቶስ] መጨመር የእግዚአብሔር ልጆች ተደርገናል—ዮሐ. 1፡12-13፤ 3፡29-30፤ ዘፍ 2፡21-23፦
   ሀ. ሔዋን ወደ ሕልውና ከመምጣቷ በፊት የአዳም የጎን አጥንት፣ የአዳም ክፍል ነበረች፤ በዚህ መገለጥ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ወደ ሕልውና ከመምጣቷ በፊት የክርስቶስ ክፍል ነበረች ማለት እንችላለን፤ የአካላችን ብልቶች የእኛ ክፍል እንደሆኑ ሁሉ የክርስቶስ ብልቶች የክርስቶስ ክፍሎች ናቸው—ቁ. 21-23፤ ኤፌ. 1፡3-6፤ 1 ቆሮ. 12፡12፤ ሮሜ 12፡5፤ ተዛ. ሐዋ 9፡5።
   ለ. ሔዋንን የአዳም አምሳያ ለማድረግ የአዳም የጎን አጥንት ወደ ሔዋን ውስጥ ሕይወት እንዳካፈለ ሁሉ፣ የክርስቶስ ዘላለማዊ፣ መለኮታዊ፣ የማይጠፋ ሕይወት የእርሱ አምሳያ ያደርገን ዘንድ ወደ እኛ ውስጥ ሕይወት ያካፍላል—ዘፍ. 2፡22፤ ዕብ. 7፡16፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ሮሜ 8፡2።

ለ. ለመባዛቱ እንደ አንድ የስንዴ ቅንጣት ወደ ምድር በመውደቅና በመሞት፣ በመለኮታዊው ሕይወቱ መለቀቅ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ ውስጠ-ነገር ሆነ—ዮሐ. 12፡24፤ ሉቃ. 12፡49-50።

ሐ. እግዚአብሔር የክርስቶስ ብዙ ወንድሞች የሆኑ ብዙ ልጆች ይኖሩት ዘንድ የእግዚአብሔር በኵር ልጅ የሆነው ክርስቶስ በትንሣኤው መለኮታዊውን ሕይወት በማካፈል የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ ውስጠ-ነገር ሆነ—1 ጴጥ. 1፡3፤ ሮሜ 8፡29፤ ዕብ. 2፡11-12።

መ. በመሰራጨቱ ለክርስቶስ መተለቅ ብዙ ፍሬ ለማፍራት በዚህም ሦስታንዱን አምላክ እንደ ሕይወታዊ አካሉ ይገልጡት ዘንድ የክርስቶስ ብዙ ወንድሞች በአጽናፍ-ዓለም ውስጥ እውነተኛ የወይን ተክል ከሆነው ከእርሱ ጋር በተጋቦ የተጋጠሙ (grafted) የእርሱ ብዙ ቅርንጫፎች ናቸው፤ የወይን ተክሉ ቅርንጫፎች እንደ የክርስቶስ የሕይወት-ጭማቂ ሕይወት-የሚሰጠውን መንፈስ በቂ አቅርቦት ሲቀበሉ፣ እንደ የውስጡ የሕይወት አቅርቦት ሞልቶ መፍሰስ ፍሬ ያፈራሉ—ዮሐ. 15፡1፣ 4-5፣ 16፤ 8፤ ሮሜ 11፡17፣ 24።

ሠ. ይህ የሦስታንዱ አምላክ ሕይወታዊ አካል የሕይወታዊ አካሉ ብዙ ብልቶች በሆኑ በብዙ ወንድሞቹ የተቀናበረ የክርስቶስ ሕይወታዊ አካል ነው—ኤፌ. 1፡22-23፤ ሮሜ 12፡5።

**II. የቤተ ክርስቲያንን ሕይወታዊ ሕልውና ማየት እና መለማመድ ያስፈልገናል—ኤፌ. 1፡17፦**

ሀ. ቤተ ክርስቲያን በአጽናፍ-ዓለም ውስጥ የምትኖረው እንደ አንዷ የእግዚአብሔር አጽናፍ-ዓለማዊ ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር አጽናፍ-ዓለማዊ መገለጥ፣ ለእግዚአብሔር ሙላት ነው—1 ቆሮ. 10፡32፤ 12፡28፤ ኤፌ 3፡19።

ለ. ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አጥቢያዊ መገለጥ ለመሆን በብዙ አጥቢያዎች ውስጥ በምድር ላይ እንደ ብዙዎቹ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እየተሰራጨች ነው—ራእ. 1፡4፣ 11፡-

1. በ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡28 ጳውሎስ ሐዋርያትን (አጽናፍ-ዓለማዊ የሆኑትን)፣ ነቢያትን እና አስተማሪዎችን (አጽናፍ-ዓለማዊም አጥቢያዊም የሆኑትን) እና ዲያቆናትን እና ሽማግሌዎችን (አጥቢያዊ የሆኑትን) ሁሉ በአንድ ላይ ያስቀምጣል፤ ይህም ማለት በዚህ ጥቅስ ላይ *ቤተ ክርስቲያን* የሚለው ቃል የሚያመለክተው አጽናፍ-ዓለማዊዋን ቤተ ክርስቲያን እና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ ነው።
2. በእግዚአብሔር ዓይኖች አጽናፍ-ዓለማዊዋ ቤተ ክርስቲያን እና ሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት "ቤተ ክርስቲያን" ናቸው፤ በሂደት ያለፈው እና አሁን-የሚያድለው ሦስታንዱ አምላክ አንድ ነው፣ እርሱ የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-ነገር ነው፤ ስለዚህ ይህች ቤተ ክርስቲያን በአጽናፍ-ዓለማዊም ሆነ በአጥቢያዊ ገጽታዋ አንድ ቤተ ክርስቲያን ናት።

ሐ. ለሕይወታዊ ሕልውናዋ ወደ የቤተ ክርስቲያን ውስጥ-መሠረታዊ ውስጠ-ነገር ስንመለስ፣ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት አንዳቸው ከሌላቸው ሊለያዩ እንደሚችሉ የሚያስተምረውን የስሕተት ትምሕርት በተሳሳተ መንገድ አንናገርም፤ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ በሂደት ያለፈው እና የሚያድለው ሦስታንዱ አምላክ ልዩና ብቸኛ አንድ ሕይወታዊ አካል ናቸው።

መ. በቅዱሳት መጽሐፍት መሠረት ተግባራዊው፣ ሰባት እጥፍ የሆነው አንድነት እኛ (1) በትምሕርት አንድ (1 ቆሮ. 4፡17፤ 7፡17፤ 16፡1፤ ሐዋ. 2፡42፤ ሮሜ 16፡17፤ 1 ጢሞ. 1፡3-4፤ 6፡3፤ ኤፌ. 4፡13-14፤ (2) በተግባራዊ ልምምድ አንድ (1 ቆሮ. 11፡16፤ 14፡33-34)፣ (3) በአሳብ አንድ (ፊልጵ. 2፡2፣ 5-8፤ 4፡2፤ 1 ቆሮ. 1፡10)፣ (4) በንግግር አንድ (ሮሜ 15፡6፤ 1 ቆሮ. 1፡10) እና (5፣ 6 እና 7) በውስጥ-ነገር፣ በውጫዊ ገጽታ እና በመገለጥ አንድ እንሆን ዘንድ ነው (ራእ. 1፡11-12)።

## III. ለሕይወታዊ ሕልውናዋ በቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ ውስጠ-ነገር እውነታ በሕይወት መንገድ ለመቆየት ባለማቋረጥ መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ (1 ጢሞ. 4፡7) እና ልባችንን ወደ ጌታ ማዞር አለብን (2 ቆሮ. 3፡16-18)፡-

ሀ. በመንፈሳችን መሠረት በሆነው በሕይወት ዛፍ ለመኖር በሕይወት መንገድ መመላለስ እንጂ በእኔነት መሠረት በሆነው በትክክል እና በስህተት የእውቀት ዛፍ ለመኖር በሞት መንገድ መመላለስ የለብንም—ዘፍ. 2፡9፤ ሮሜ 8፡4፣6፤ 2 ቆሮ. 2፡13፤ ማቴ. 16፡24።

ለ. በሕይወት መንገድ የምንቆየው ጌታን ፈጽሞ በመውደድ ነው፤ በጌታ ማመን እርሱን እንደ ሕይወት መቀበል ነው፤ ጌታን መውደድ እርሱን እንደ ሕይወት መደሰት ነው—ማር. 12፡30፤ መኃ. 1፡4።

ሐ. በእኛ እና በጌታ መካከል ያለው ፍቅር በአሳቦቻችን ላይ ይመረኮዛል፡-

1. ክርስቶስን ለእርሱ ባለን ተገቢ <u>ፍቅር</u> እንደሰተው ዘንድ በ 2ኛ ቆሮንቶስ 11፡2 ጳውሎስ እንደ ንጽሕት ድንግል እኛን ለክርስቶስ ለማቅረብ ለአንድ ወንድ እንዳጨን ይናገራል፤ ከዚያም በቁጥር 3 ላይ <u>አሳባችን</u> ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ሊበላሽ እንደሚችል ጳውሎስ ይነግረናል።
2. ከሰው የአሳብ ችግሮች ጋር የተያያዙት የሚከተሉት ምልክቶች ሁሉ ክርስቶስን እንደ ሕይወት ለመደሰት እንቅፋቶች ናቸው፡-

   ሀ. የመጀመሪያው ከሰው የአሳብ ችግሮች ጋር የተያያዘው ምልክት የደነዘዙ አሳቦች ያለው መሆን ነው—3፡14።
   ለ. ሁለተኛው ከሰው የአሳብ ችግሮች ጋር የተያያዘው ምልክት በሰይጣን መታወር ነው—4፡4።
   ሐ. ሦስተኛው ከሰው የአሳብ ችግሮች ጋር የተያያዘው ምልክት አመጽ ነው—10፡4-5።
   መ. አራተኛው ከሰው የአሳብ ችግሮች ጋር የተያያዘው ምልክት መበላሸት ነው—11፡3።
3. እንዲህ ብለን መጸለይ አለብን፣ "ኦ ጌታ፣ አሳቦቼን መርምር፣ በአንተ ላይ ብቻ እና ሙሉ በሙሉ በአንተ ላይ ማተኮር እንዲችሉ አሳቦቼን አድን"—ሮሜ 8፡6፤ መዝ. 139፡23-24።
4. ክርስቶስን እንደ የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-ነገር ለመደሰት በነገር ሁሉ ለጌታ ፊተኛውን ስፍራ በመስጠት ለጌታ የሚቃጠል ፍቅር ሊኖረን ይገባል—ራእ. 2፡4-5፣ 7፤ ቆላ. 1፡18፤ ሮሜ 12፡11፤ 2 ጢሞ. 1፡6-7።

መ. በሕይወት በማደጋችን በሕይወት ለሆነው ለእግዚአብሔር ግንባታ በሕይወት ፍሰት ክርስቶስን እንደ ሕይወት ዛፍ በመደሰት በሕይወት መንገድ፣ በሕይወት መስመር እና ሕይወትን በመጠበቅ ውስጥ እንቆይ ዘንድ የአምላካችንን ምሕረት የተሞሉ ርኅራኄዎችን ባለማቋረጥ እንቀበል (ዕብ. 4፡16፤ ሉቃ. 1፡78-79)፤ ይህ ለቤተ ክርስቲያን ሕይወታዊ ሕልውና በቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ ውስጠ-ነገር ውስጥ ለመቆየታችን ነው (ዘፍ. 2፡9፤ ራእ. 22፡1-2፤ ሮሜ 8፡6፤ ኤፌ. 4፡15-16፤ ቆላ. 2፡19፤ ዮሐ. 6፡57፣ 63፤ 7፡38-39፤ 20፡22)።

© 2021 Living Stream Ministry